የኢትዮጵያ
ቡናና ሻይ ባለስልጣን
ETHIOPIAN
COFFEE AND TEA AUTHORITY

መመሪያ ቁጥር ፱፻፹፯/፪ሺ፲፮

የውጭ ንግድ ደረጃ ያለውን እሴት የተጨመረበት ቡና በሃገር ውስጥ በውጭ ምንዛሬ ለመሸጥ የሚያስችል የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር ፱፻፸፰/፪ሺ፲፮

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን በቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፩/፪ሺ፱ አንቀጽ ፷፬ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የውጭ ንግድ ደረጃ ያለውን እሴት የተጨመረበት ቡና በሀገር ውስጥ በውጭ ምንዛሬ ለመሸጥ የሚያስችል የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር ፱፻፸፰/፪ሺ፲፮ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

፩/ "ደንብ " ማለት የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ደንብ ቁጥር ፬፻፴፫/፪ሺ፲፩ ማለት ነው፤

፪/ "እሴት የተጨመረበት ቡና" ማለት በተፈቀደ የቴክኒክ አሰራር መሰረት ጥሬ ቡና ተቆልቶ ወይም ተቆልቶና ተፈጭቶ ወይም ወደ ተለያየ የቡና ምርት ውጤት አይነት የተለወጠ ነው፤

፫/ "የውጭ ሃገር ምንዛሬ" ማለት ኢትዮጵያ በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያለው የውጭ ሃገር መገበያያ ገንዘብ ነው፤

፬/ "ሻጭ" ማለት የውጭ ደረጃ ቡና ቆልቶና ፈጭቶ የላኪነት ብቃት ማረጋገጫና የውጭ ንግድ ደረጃ ቡናን በሃገር ውስጥ ለመሸጥ ልዩ ብቃት ማረጋጋጫ ያለው  ሰው ነው፤

፭/ "ገዢ" ማለት የውጪ ሃገር ጎብኚዎችና መንገደኞች ፣ ኢምባሲዎች፣ የአለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ሁነት ተሳታፊዎች እና ሌሎች በህጋዊ የውጭ ምንዛሬ የወጭ ንግድ ቡናን መግዛት የሚችል ሰው ነው፤

፮/ "የክፍያ ማሽን" ማለት የግብይት ክፍያን በክሬዲት ካርድ ወይም በተመሳሳይ ዘዴ ማከናወን የሚያስችል ማሽን ነው፤

፯" ክሬዲት ካርድ" ማለት ከገዢው ውጪ ምንዛሬ ሂሳብ ቁጥር ጋር የተገናኘ ዕቃና አገልግሎትን ለመግዛት የሚያገለግል የክፍያ ካርድ ነው፤

፰/ "በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ" ማለት ዘመናዊ ኤሌክትሮኒክሰ የገንዘብ የክፍያ ዘዴ ማለት ነው።

## ፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ የውጭ ንግድ ደረጃ ያለው እሴት የተጨመረበት ቡና በሃገር ውስጥ በውጭ ምንዛሬ በሚደረግ ግብይት ወይም ጥራት ቁጥጥር ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

# <u>ክፍል ሁለት</u>

# <u>የግብይት አሰራር</u>

## ፬. <u>የግብይት አሰራር</u>

በደንቡ አንቀፅ ፱ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ፦

፩/ የውጭ ንግድ ደረጃ ያለው ዕሴት የተጨመረበት ቡና ግብይት በሻጭና  በገዢ መካከል ይፈጸማል፤

፪/ ግብይቱ በዚህ መመሪያ ተለይተው በተፈቀዱ ቦታዎች ብቻ ይከናወናል፤

፫/ ገዢው የሽያጭ ክፍያውን የሚፈጽመው በክሬዲት ካርድ ወይም በተመሳሳይ ዘዴ ወይም በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ መሆን አለበት፤

፬/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፫ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ግብይቱ በጥሬ ገንዘብ ሊከናወን የሚችለው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በቁጥጥርና በክትትል የእያንዳንዱን ሽያጭና ክፍያ ሲያረጋግጥ፤

ብቻ ነው፡፡

## ፭. የግብይት ሥፍራዎች

ዕሴት የተጨመረበት የውጪ ንግድ ደረጃ ያለው ቡና በውጭ ምንዛሬ በሃገር ውስጥ ሽያጭ የሚከናወንበት ቦታ፡-

፩/ በህግ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በመባል የተካተቱ ሆቴሎች፣ሞቴሎች ፣ ሎጆች፣ፔኒሲዮኖች፣ ሬስቶራንቶችና ካፌዎች፤

፪/ በኢትዮጵያ ኤርፖርቶች፤

፫/ በኢትዮጵያ የቱሪሰት ማዘውተሪያ ፓርኮች፤

፬/ አህጉርና ዓለም አቀፍ የኹነት ማካሄጃ በሆኑ ቦታዎች፤

ናቸው፡፡

## ፮. የሻጭ ግዴታ

ማንኛውም ሻጭ፡-

፩/ የውጭ ንግድ ደረጃ ያለውንና ዕሴት የተጨመረበትን ቡና በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፭ ሥር በተዘረዘሩት ሥፍራዎች ብቻ ግብይት የማካሄድ፤

፪/ ዕለታዊ ግዢና ሽያጭ መጠን፣ደረጃና ዋጋ፣መረጃ መዝግቦ የመያዝና በየሳምንቱ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ ፤

፫/ ምርት ለማጓጓዝ የሚያስችል የመሸኛ ደብዳቤ የመያዝ፤

፬/ የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበትን ምርት ያለመሸጥ፤

፭/ በባለሥልጣኑ ካስመዘገበው የቅይጥ ቡና ዝግጅትና የንግድ ስያሜ መብት ውጭ አንዱን ዓይነት ቡና ከሌላ ዓይነት ጋር ሳይቀይጥ ወይም ሳይደባልቅ ቡናው የተመረተበት አካባቢ ባህሪና ስያሜ ጠብቆ ለግብይት የማቅረብ፤

፮/ ከሳምንታዊ ዝቅተኛ የቡና መሸጫ ዋጋና ከዚያ በላይ የመሸጥ፤

ግዴታ አለበት፡፡

## ፯. የገዢ ግዴታ

ማንኛውም ገዢ፡-

፩/ ለሚገዛው ዕሴት የተጨመረበት የውጭ ንግድ ደረጃ ቡና በህጋዊ የውጭ ምንዛሬ የመክፈል፤

፪/ በዚህ መመሪያ በተፈቀዱ የመገበያያ ሥፍራዎች ብቻ የመግዛት፤

፫/ ለገዛው ዕሴት የተጨመረበት የውጭ ንግድ ደረጃ ቡና መጠን ከገዛበት መደብር ህጋዊ ደረሰኝ ይዞ የመንቀሳቀስ፤

ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት

## የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ

## ፰. የሽያጭ መደብር የቴክኒክ መስፈርት

ለሽያጭ የሚያስፈልግ መደብር፡-

፩/ እሴት የተጨመረበት የውጭ ንግድ ደረጃ ያለው ቡና በውጭ ምንዛሬ መሽጫነት የሚያገለግል ጥራቱን ለመጠበቅ የሚያስችል አየር ማስገቢያና ማስወጪያ ያለው እና ጣዕም ከሚቀይሩ ባዕድ ነገሮች የጸዳ ክፍል ያለው፤

፪/ ትክክለኛነቱ በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ ለቡና ክብደት መለኪያ የሚያገለግል ሚዛን ያለው፤

፫/ እሴት የተጨመረበት ቡና ለማሸግ የሚያችል ቁሳቁስ ያሟላ፤

፬/ የኢትዮጵያ ቡናን ለማስተዋወቅ የሚያስችሉ ባነሮች፣ ብሮሽሮች፣ በራሪ ወረቀቶችና ሌሎች የማስታወቂያ መሳሪያዎች የተዘጋጀለት፤

፭/ እሴት የተጨመረበትን ቡና በጊዜያዊነት ለማቆዬት የሚውል ለቡና ተስማሚ የሆነ መደርደሪያ የተዘጋጀለት፤

፯/ ክፍያን በኤሌክትሮኒክስ ወይም በክሬዲት ካርድ ወይም በዴቢት ካርድ ለመፈጸም የሚያስችል መሳሪያ የተሟላለት፤

መሆን አለበት ።

## ፱. <u>የውጭ ንግድ ደረጃ ያለው ዕሴት የተጨመረበት ቡና ሻጭ ብቃት ማረጋገጫ</u>

ለውጭ ንግድ የተዘጋጀን ቡና ለሃገር ውስጥ ለመሸጥ የሚፈቀድለት ሰው፡-

፩/ የውጪ ቡና ቆይነት ብቃት ማረጋገጫ ያለው፤

፪/ በዚህ መመሪያ መሰረት የቴክኒክ መስፈርቶች ያሟላ መሸጫ መደብር በባለቤትነት ወይም አግባብ ባለው አካል በጸደቀ የኪራይ ውል የያዘ፤

፫/ በሃገር ውስጥ በተፈቀደ የውጭ ምንዛሬ ለመሸጥ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ተመዝግቦ ዕውቅና ያገኘ፤

፬/ የተሸጠው ቡና ዓይነት፣ መጠን፣ የገንዘቡ ልክ በውጭ ምንዛሪና መሸጫ ቦታው ተገልጾ ደረሰኝ ለመስጠት የሚያስችል አሰራር የዘረጋ፤

፭/ ያስመዘገበው የንግድ ወይም የሥራ አድራሻ በቀየረ ጊዜ አዲሱን አድራሻ የሚያሳውቅ፤

መሆን አለበት።

## ፲. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

በዚህ መመሪያ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት፡-

፩/ አመልካቾች እንዲሞሉት በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ አለበት፤

፪/ ከተሞላው ቅጽ ጋር በዚህ መመሪያ የተገለጹትን መስፈርቶች ስለሟሟላቱ የሚያሳዩ ማስረጃዎችን አያይዞ ማቅረብ አለበት፤

፫/ በባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው የሥራ ኃላፊ የቀረበውን ማማልከቻ ተቀብሎ የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብ ለሚመለከተው ባለሙያ ይመራል፤

፬/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፫ የተመራለት ባለሙያ አመልካቹ ያቀረባቸውን ሰነዶች በቴክኒክ መስፈርቱ መሠረት መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤ በአካል በመስክ ተገኝቶ

ማረጋገጥ ሲያስፈልገው ይህንኑ ያረጋግጣል። የማጠቃለያ የግመገማ ቅጽ ሞልቶ ለሥራ ኃላፊው ለውሳኔ ያቀርባል፤

፫/ የሥራ ኃላፊው የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ በመመልከት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፬/ ባለሙያው ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚሟላ የቴክኒክ መሥፈርት ጉድለት ያለው ከሆነ ለአመልካቹ በአምስት የሥራ ቀናት እንዲያሟላ እድል ይሰጣል፤

፭/ በባለስልጣኑ  የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጠው የሥራ ኃላፊ ማመልከቻውን ውድቅ ካደረገ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በ፲፫ ቀን ውስጥ የክልከላው ምክንያት ተጠቅሶ ላመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤

፰/አመልካቹ በብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሰጪ ክፍሉ የተሰጠውን ውሳኔ የሚቃወም ከሆነ ቅሬታውን በጽሁፍ ለባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ በ፲፫ የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፤

፱/ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ በ ፲ የሥራ ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

፲/ ቅሬታ አቅራቢው የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማማ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት በ፴ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ማመልከት ይችላል።

## ፲፩. <u>የብቃት ማረጋገጫ ዕድሳት</u>

፩/ ማንኛውም የውጪ ንግድ ደረጃ ያለው ዕሴት የተጨመረበት ቡና ሻጭ ብቃት ማረጋገጫ  በየዓመቱ ማሳደስ አለበት።

፪/ የብቃት ማረጋገጫ እድሳት ቅጽ በመሙላት በደንቡና በዚህ መመሪያ የተገለጹትን መስፈርቶች ስለማሟላቱ የሚያሳዩ ማስረጃዎችን አያይዞ ማቅረብ አለበት።

፫/ የዘመኑን ግብር ክሊራንስ ማቅረብ አለበት።

፬/ ያለፈውን ዓመት የቡና ግዢና ሽያጭ በብሔራዊ ባንክ የተረጋገጠ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

፫/ አሳማኝ ምክንያት መኖሩን በማስረጃ አስደግፎ ካልቀረበ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ወደ ሥራ ያልገባ ሰው ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማሳደስ አይችልም፡፡

፬/ ቀድም ብሎ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወስዶ የአድራሻ ለውጥ ያደረገ እና ይህንኑ ያሳወቀ እንደሆነ በባለስልጣኑ ታይቶ በተለወጠው አድራሻ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጠዋል፡፡

፭/ በግብይት ሂደት ህገ ወጥ ድርጊት ውስጥ መሳተፉ የተረጋገጠበት ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አይታደስለትም፡፡

**፲፪. <u>የብቃት ማረጋገጫ ዕገዳ</u>**

በደንቡ ላይ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን የሚያሳግዱ ጥፋቶች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

፩/ የብቃት ማረጋገጫ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊታገድ ይችላል፡-

ሀ) በባለስልጣኑ የተጠየቀውን መረጃ ወይም ሰነድ በወቅቱና በአግባቡ ያላቀረበ ከሆነ፣

ለ) ያስመዘገበውን የንግድ ወይም የሥራ አድራሻ ለባለስልጣኑ ሳያሳውቅ የቀየረ እንደሆነ፤

፪/ ባለስልጣኑ ለእገዳው ምክንያት የሆኑትን ጉድለቶች መዝግቦ ጉድለቶቹ እንዲስተካከሉ በጽሁፍ አሳውቆ እስከ ፴ ቀናት ብቃት ማረጋገጫውን አግዶ ሊያቆይ ይችላል፤ እገዳውንም ለሚመለከታቸው አካላት በጽሁፍ ያሳውቃል፤

፫/ ብቃት ማረጋገጫ የታገደበት ሰው በተሰጠው የጊዜ ገደብ ጉድለቶቹን አስተካክሎ በጽሁፍ ለባለስጣኑ  ካሳወቀና ይህም ከተረጋገጠ እገዳው ወዲያውኑ ይነሳል፤ ለሚመለከተው አካልም በጽሁፍ ይገለጻል፡፡

**፲፫. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ</u>**

በደንቡ ላይ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን የሚያሰርዙ ጥፋቶች እንደተጠበቁ ሆነው ፡-

፩/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሰረዝ ይችላል፡-

ሀ) የቡና ንግድ ሥራውን በራሱ ፍቃድ የተወ እንደሆነ ወይም

ለ) የብቃት ማረጋገጫው የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ዓላማ ውጪ ሲጠቀምበት የተገኘ እንደሆነ ነው፤

፪/ ባለስልጣኑ የስረዛውን ምክንያት ጠቅሶ ለባለጉዳዩና ለሚመለከታቸው አካላት በጽሁፍ ያሳውቃል፤

፫/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰረዘበት ሰው የሥራ ክፍሉ የሰጠውን ውሳኔ የሚቃወም ከሆነ ቅሬታውን በጽሁፍ ለባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ በ ፲ የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላል፤

፬/ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ በ ፭ የሥራ ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

፭/ ቅሬታ አቅራቢው በባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማማ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## የጥራትና ግብይት ቁጥጥር አሰራር

### ፲፬. የጥራት ቁጥጥር አሰራር

፩/ የመሸጫ መደብሩ የቡናውን ጥራት ከሚያጓድሉ ነገሮች የጸዳ ስለመሆኑ በባለሰልጣኑ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፪/ ለሀገር ውስጥ በውጭ ምንዛሬ የሚቀርበው እሴት የተጨመረበት ቡና ዝግጅት፣ ክምችት፣ እሽጋ እና በሚጓጓዝበት ወቅት ጥራትን ከሚያጓድሉ ነገሮች የጸዳ ስለመሆኑ በባለሰልጣኑ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፫/ ለሀገር ውስጥ በውጪ ምንዛሬ የሚቀርበው እሴት የሚጨመርበት ቡና ለውጪ የጥራት ደረጃ የሚመጥን መሆኑ በቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፍኬሽን ማዕከል መረጋገጥ አለበት፡፡

### ፲፭. የግብይት ቁጥጥር አሰራር

፩/ ለሀገር ውስጥ በውጭ ምንዛሬ የሚቀርበው ቡና ከመቆያ ቦታ ወደ ተፈቀደ መሸጫ መደበር ሲጓጓዝ የምርቱ መጠን፣ የሚጓጓዝበት መነሻና መድረሻ፣ የሚጓጓዝበትን ቀን፣ የተሽከርካሪ ሰሌዳ፣ የአሽከርካሪው ስም የሚገልጽ በባላስልጣኑ የተሠጠ የመሸኛ ሰነድ ያስልጋል፡፡

፪/ ግብይቱ ይህ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ስለመፈጸሙ በየጊዜው በባለሰልጣኑ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

፫/ ግብይት የተፈጸመበት ቡና አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ከተሸጠ በኋላ በሀገሪቱ ህጋዊ የመውጫ በሮች ሲጓጓዝ በባለሰልጣኑ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፮. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### ፲፯. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፫/፪ሺ፲፪ መሰረት በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በፍትህ ሚኒስቴር እና በባለስልጣኑ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዱኛ ደበላ (ፒኤች.ዲ)

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን

መስከረም ፪ሺ፲፮ ዓ.ም